- ኢየሱስን ለመግደል የፈለጉት እነማን ነበሩ?

- የካህናት አለቆችና ፈርሳውያን።

- የካህናት አለቆችና ፈርሳውያን ኢየሱስን እንዲገድሉት የመራቸው ማን ነበር?

- ሰይጣን

- የካህናት አለቆችና ፈርሳውያን ኢየሱስን ለመግደል የፈለጉት ለምን ነበር?

- ክፉዎች ስለነበሩ ነው።

- እነርሱ ኢየሱስን ሳይሆን ሰይጣንን ስለታዘዙ ነው።

- እናንተስ ማንን ነው የምትታዘዙት? ኢየሱስን ወይስ ሰይጣንን?



## ትምህርት 61

1. እረኞች በጎቻቸውን በሌሊት የሚጠብቁት እንዴት ነበር?

ሀ- ከመምሸቱ በፊት የድንጋይ ወይም የእሾህ ካብ ሠርተው አንድ በር ያደርጉ ነበር::

2. ካቡ ተሠርቶ ሲያልቅ እረኛው በጎቹን በካቡ ውስጥ አስገብቶ እርሱ የሚተኛው የት ነው?

ሀ- እረኛው መግቢያ በር ላይ ይተኛል::

3. እረኛው መግቢያ በር ላይ የሚተኛው ለምንድን ነው?

ሀ- በካቡ ውስጥ ያሉትን በጎች ለመከላከል::

4. ኢየሱስ “እኔ የበጎች በር ነኝ” ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ- ኢየሱስ እርሱ ከሞት የምንድንበት መንገድ መሆኑን መናገሩ ነው::

5. የኢየሱስ በጎች እነማን ናቸው?

ሀ- ኃጢአታቸው ሞት እንደሚያመጣባቸው የሚያውቁና ከኃጢአታቸው እንዲያድናቸው ኢየሱስን የሚጠሩት ናቸው።

6. አንዳንድ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚያስገቡ ብዙ በሮች አሉ ይላሉ ይህ እውነት ነውን?

ሀ- አይደለም ውሸት ነው።

7. በኖኅ መርከብ አንድ በር መኖሩ ስለ ኢየሱስ ምን ያሳስበናል?

ሀ- የኖኅ መርከብ አንድ በር ብቻ እንደነበረው ሁሉ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያስገባው ብቸኛው በር ኢየሱስ መሆኑን ነው።

ለ- በአንዱ በር ወደ ኖኅ መርከብ የገቡት ከሞት እንደዳኑ ሁሉ በኢየሱስ የሚያምኑት ሁሉ ከሞት እንደሚድኑ::

8. ሊሰርቅ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ የሚመጣው ሌባ ማን ነው?

ሀ- ሰይጣን::

9. ኢየሱስ በጎቹን በጣም ስለምወድ ምን ላደርግላቸው ፈቃደኛ ነኝ አለ?

ሀ- “ልሞትላቸው ፈቃደኛ ነኝ” አለ::

- አንድ ቀን በቢታኒያ የሚኖር የኢየሱስ ወዳጅ አልዓዛር ታመመ።

ዮሐንስ 11:1-6

1- በማርያምና በእህቷ በማርታ መንደር በቢታኒያ ይኖር የነበረው አልዓዛር ታሞ ነበር::

2- ይህች ወንድሟ አልዓዛር የታመመባት ማርያም በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ እግሩን በጠጕራ ያበሰችው ነበረች::

3- እህታማቾቹም «ጌታሆይ የምትወደው ታሞአል»ብለው መልእክት ላኩበት::

4-ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ«ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት የሚያደርስ አይደለም” አለ።

5-ኢየሱስ ማርታን እህቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር::

6- ሆኖም አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቆየ።

- አልዓዛር ሲታመም ማርያምና ማርታ ከቢታኒያ በጣም ርቆ ለነበረው ኢየሱስ መልእክት ላኩበት::



- አልዓዛር ከሞት ተነሣ?

- አዎን

- ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት የቻለው እንዴት ነው?

- ሕያው ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

- ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ለማስነሣት የወሰነው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ፥ እግዚአብሔር በሞትም ላይ እንኳን ስልጣን እንዳለው ለሰዎች ሁሉ ለማሳየት ስለፈለገ ነው።

- ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ካስነሣው በኋላ ሰዎች ምን አሉ?

ዮሐንስ 11፥45-48

45- ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፥ ኢየሱስ ያደረገውን ካዩት አይሁድ ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

46-አንዳዶች ግን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ለፈርሳውያን ተናገሩ።

47- ከዚያም የካህናት አለቆችና ፈርሳውያን የአይሁድን ሸንጎ ስብሰባ ጠሩ። እነርሱም እንዲህ አሉ፤ “ይህ ሰው ብዙ ተአምራዊ ምልክቶች እያደረገ ስለሆነ ምን ብናደርግ ይሻላል?

48- እንዲሁ ብንተወው ሰው ሁሉ በእርሱ ያምናል፤ ሮማውያን መጥተው ሥፍራችንና ሕዝባችንን ይወስዱብናል። ”

- ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ሰላስነሣው አንዳንዶች ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አመኑ።

- ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ስላስነሣው አንዳንዶች ሄደው ኢየሱስን ለመግደል አሤሩ።

-እግዚአብሔር ሰዎች ሲጎዱ ያዝናል።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሲታመሙ ያዝናል።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለፈጠረና ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ ነው።

- ቀጥሎስ ኢየሱስ ለሕዝቡ ምን አለ?

ዮሐንስ 11፡39- 44

39- እርሱም “ድንጋዩን አንሱት” አለ። የሟቹም እህት ማርታ “ጌታ ሆይ፤ አሁንማ አራት ቀን ስለቆየ ይሸታል” አለችው።

40- ኢየሱስም “ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርኩሽም” አላት።

41- ስለዚህ ድንጋዩን አነሡ። ኢየሱስም ወደ ላይ ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ “አባት ሆይ ስለሰማኸኝ አመስግንሃለሁ።

42- ሁል ጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ፤ ይህን መናገሬ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ ነው።”

43- ኢየሱስም ይህንን ካለ በኋላ በታላቅ ድምጽ “አልዓዛር፥ ና ውጣ” ብሎ ተጣራ።

44- የሞተውም ሰው እጅና እግሩ በቀጭን ስስ ጨርቅ እንደተጠቀለለ፥ ፊቱም በሻሽ እንደተጠመጠመ ወጣ። ኢየሱስም መግነዙን ፊቱትና ይሂድ” አላቸው።

- ኢየሱስ ምን አደረገ?

- ኢየሱስ በመቃብሩ መግቢያ በር ላይ ቆሞ አልዓዛር ከሞት እንዲነሣ አዘዘው።



- ኢየሱስ ስለ አልዓዛር ህመም ምን አለ?

- ኢየሱስ “የአልዓዛር ህመም ለሞት የሚያበቃ ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ነው” አለ::

- ኢየሱስ የአልዓዛርን መታመም ቢሰማም በነበረበት ስፍራ ለተጨማሪ ሁለት ቀን ቆየ::

- ኢየሱስ የአልዓዛርን መታመም እንደሰማ ወዲያውኑ ያልሄደው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ አዳኝ አምላክ በመሆኑ ታላቅ ኃይሉን ሊያሳይ ስለፈለገ ነበር።

- ኢየሱስ በርቀት ሆኖ አልዓዛርን መፈወስ ይችል ነበር?

- አዎን::

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ተናገራቸው።

ዮሐንስ 11:7-8 እና 11-16

7- ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን «ወደ ይሁዳ እንመለስ» አላቸው።

8- እነርሱም «መምህር ሆይ ከጥቂት ጊዜ በፊት አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩህ እየፈለጉህ ነበር እንደገና ወደዚያ ትሄዳለህን»? አሉት።

11- ይህን ከነገራቸው በኋላ፥ «ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል እኔም ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ» አላቸው።

12- ደቀመዛሙርቱ፥ «ጌታ ሆይ» ተኝቶ ከሆነስ ይድናል» አሉት።

13- ኢየሱስ ይህን የነገራቸው ስለ ሞቱ ነበር፤ ደቀመዛሙርቱ ግን እንቅልፍ ስለ መተኛቱ የተናገረ መሰላቸው።

14- ስለዚህም በግልጽ እንዲህ አላቸው፤

15- “አልዓዛር ሞቶአል፤ ታምኑ ዘንድ በዚያ ባለመኖሬ ስለእናንተ ደስ ይለኛል፤ አሁን ግን ወደ እርሱ እንሂድ።

16- ከዚያም ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ ለተቀሩት ደቀመዛሙርት፥ “እኛም ሄደን ከእርሱ ጋር እንሙት” አላቸው።

- ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ “ወደ ይሁዳ እንመለስ” ሲላቸው ደቀመዛሙርቱ ለምን ፈሩ?

- ምክንያቱም በይሁዳ የነበሩት አይሁድ ኢየሱስን በድንጋይ ሊወግሩት ይፈልጉ ስለነበር ነው።

- ኢየሱስ አልዓዛር እንደ ሞተ ሲናገር ደቀመዛሙርቱ አልገባቸውም ነበር።

- ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ከአልዓዛር ጋር እንዲሆን ለአይሁዶች ራሱን አሳልፎ ሊሰጥ የፈለገ መስሏቸው ነበር።

- ኢየሱስ እንዲህ አላለም።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ወደ ቢታንያ ሲደርሱ ምን ተፈጸመ?

ዮሐንስ 11፥17–22

17- ኢየሱስ ሲደርስ አልዓዛር ከተቀበረ አራት ቀን ሆኖት ነበር።

18- ቢታንያ ከኢየሩሳሌም አሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ትርቅ ነበር።

19- ብዙዎች አይሁድ ማርታንና ማርያምን ስለ ወንድማቸው ሞት ሊያጽናኗቸው መጥተው ነበር።

20- ማርታ የኢየሱስን መምጣት ሰምታ ልትቀበለው ወጣች። ማርያን ግን በቤት ቀርታ ነበር።



29- ማርያም ይህንን እንደሰማች ፈጥና ተነሥታ ወደ እርሱ ሄደች።

30- በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፥ ማርታ እርሱን በተቀበለችበት ቦታ ነበር እንጂ ገና ወደ መንደር አልገባም ነበር።

31- ማርያምን ሲያጽናኑ በቤት ውስጥ የነበሩ አይሁድም፤ ብድግ ብላ መውጣቷን ሲያዩ፥ ወደ መቃብሩ ሄዳ የሚታለቅስ መስሎአቸው ተከተሏት።

32- ማርያምም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቦታ ደርሳ እንዳየችው እግሩ ላይ ተደፍታ “ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባልሞተ ነበር” አለችው።

33- ኢየሱስም እርሷ ስታለቅስ፥ ተከትለዋትም የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ መንፈሱ በኀዘን ታውኮ፥

34- “የት ነው ያኖራችሁት” ሲል ጠየቀ። እነርሱም “ጌታ ሆይ መጥተህ እይ?” አሉት።

35- ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ።

36- አይሁድም “እንዴት ይወደው እንደነበር አያችሁ” አሉ።

37- ከእነርሱ አንዳዶች ግን “የዐይነ ስውሩን ዐይን የከፈተ፥ ይህም ሰው እንዳይሞት ማድረግ አይችልም ነበር?” አሉ።

38- ኢየሱስ ዳግመኛ ልቡ በኀዘን ተነክቶ ወደ መቃብሩ መጣ መቃብሩም በድንጋይ የተገጠመ ዋሻ ነበር።

- ኢየሱስ ወደ አልዓዛር መቃብር ሲመጣ ያለቀሰው ለምን ነበር?

- ሌሎች ሰዎች ሲያለቅሱ አይቶ ስላዘነ ነበር።

- እግዚአብሔር በዓለም ላይ ኃጢአት በመኖሩ ያዝናል።

- እግዚአብሔር በዓለም ላይ ሞት በመኖሩ ያዝናል።

- ኢየሱስ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ቢሞት እንኳን ህያው ይሆናል አለ።

- ሰው ከሞተ በኋላ በሕይወት የሚኖረው እንዴት ነው?

- ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ በእርሱ የሚያምኑት የስጋ ሞት ቢሞቱም እንኳን ዘላለማዊ ሞት አይሞቱም ማለቱ ነበር።

- ኢየሱስ በእርሱ የሚያምኑ በስጋ ቢሞቱም እንኳን ነፍሳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ትሄዳለች አለ።

- ከዚያስ ማርታ ለኢየሱስ ምን መለሰችለት?

ዮሐንስ 11፥27

27- እርሷም "አዎን ጌታ ሆይ፥ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አምናለሁ" አለችው።

-ማርታ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን አምናለች?
-አዎን

-ከዚያ ማርታ እህቷን ማርያምን ጠራቻት።

ዮሐንስ 11፥28-38

28- ይህን ካለች በኋላ፥ ተመልሳ እህቷን ማርያምን ለብቻዋ ጠርታ "መምህሩ መጥቷል፤ ይፈልግሻልም" አለቻት።



21- ማርታም ኢየሱስን እንዲህ አለችው:- "ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፥ ወንድሜ ባልሞተ ነበር።

22- አሁንም ቢሆን የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ።"

- የአልዓዛር እህት ማርታ ለኢየሱስስ ምን አለች?

- ማርታ ኢየሱስ በዚያ ቢሆን ኖሮ አልዓዛር አይሞትም ነበር አለች።

- ማርታ አልዓዛር በሕይወት ሳለ ኢየሱስ በዚያ ቢሆን ኖሮ አልዓዛርን ይፈውስ ነበር ብላ አሰበች።

- ከዚያስ ኢየሱስ ማርታን ምን አላት?

ዮሐንስ 11፥23-24

23- ኢየሱስም "ወንድምሽ ይነሣል " አላት።

24- ማርታም "በመጨረሻ ቀን በትንሣኤ እንደሚነሣ አውቃለሁ" አለችው።

- ኢየሱስ ለማርታ ወንድሟን አልዓዛርን ከሞት እንደሚያስነሣው ነገራት።

- ማርታ ምን እንዳለ ገብቶአታል?

- አልገባትም።

- ማርታ ያሰበችው ኢየሱስ በመጨረሻው ቀን አልዓዛርን ከሞት እንደሚያስነሣው ነው።

- ኢየሱስ ያለው ይህንን ነበር?
- አልነበረም።

- ማርታ ለኢየሱስ አልዓዛርን በመጨረሻው ቀን ከሞት እንደሚያስነሣው ነገረችው።

- ማርታ የመጨረሻ ቀን ስትል ምን ማለቷ ነበር?

- የመጨረሻ ቀን በዘመን ፍጻሜ የሞቱት ሰዎች ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት የሚሸጋገሩበት ጊዜ ነው።

- የመጨረሻ ቀን እግዚአብሔር ይፈርድባቸው ዘንድ የሞቱትን ሁሉ ያስነሳል።

- በመጨረሻ ቀን እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ስለሰሩት ኃጢአት ይፈርድባቸዋል።

- ኢየሱስ ለማርታ ምን መለሰላት?

ዮሐንስ 11፡25ሀ

25- ኢየሱስ እንዲህ አላት፤ “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ።”

- ኢየሱስ ለማርታ ምን አላት?

- ኢየሱስ ትንሣኤና ሕይወት መሆኑን ነገራት።



- ኢየሱስ ማርታን አልዓዛር ከሞት ለመነሣት የመጨረሻውን ቀን መጠበቅ የለበትም አላት።

- አልዓዛር ከሞት ለመነሣት የመጨረሻውን ቀን መጠበቅ የሌለበት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ትንሣኤና ሕይወት የሆነው ኢየሱስ በዚያ ስለነበር ነው።

- ኢየሱስ ለሞቱት እንኳን ሕይወት የመስጠት ኃይል አለው።

- ሰይጣንና አጋንንቱ ለሙታን ሕይወትን መስጠት ይችላሉ?
- አይችሉም።

- መላእክት ለሙታን ሕይወትን መስጠት ይችላሉ?
- አይችሉም።

- ለሙታን ሕይወትን መስጠት የሚችለው ማን ብቻ ነው?

- አምላክ የሆነው ኢየሱስ ብቻ ነው።

- ቀጥሎ ኢየሱስ ማርታን ምን አላት?

ዮሐንስ 11፡25ለ-26

25- “በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳን በህይወት ይኖራል፤
26- በእኔ የሚኖር የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህንን ታምኛለሽን?”